'እስክታምኑ ድረስ ጀነት አትገቡም። እስክትዋደዱ ድረስም አታምኑም። የፈፀማችሁት ጊዜ የምትዋደዱበትን አንዳች ነገር ልጠቁማችሁን? በመካከላችሁ ሰላምታን አሰራጩ።'

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ 'እስክታምኑ ድረስ ጀነት አትገቡም። እስክትዋደዱ ድረስም አታምኑም። የፈፀማችሁት ጊዜ የምትዋደዱበትን አንዳች ነገር ልጠቁማችሁን? በመካከላችሁ ሰላምታን አሰራጩ።'" [ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከአማኞች በስተቀር ማንም ጀነት እንደማይገባ፤ ከፊሉ ከፊሉን እስኪወድ ድረስም ኢማን እንደማይሞላና የሙስሊሙ ማህበረሰብ ሁኔታም እነደማይስተካከል ገለፁ። ከዚያም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በርሱ አማካኝነት ውዴታ የሚዳረስበትን በላጭ ነገር ጠቆሙ። እርሱም: በሙስሊሞች መካከል አላህ ለባሮቹ ሰላምታ መለዋወጫ ያደረገውን ሰላምታን ማሰራጨት ነው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/3361